# በሜሪላንድ አውራ ጎዳና ላይ የሚገኘው የካውንስሉ ቢሮ ሕንፃ ላይ የሚገኘው ህዝባዊ መግቢያ በር ከጁላይ 17 ቀን ጀምሮ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ዋና መግቢያ በር ተዘዋውሯል

## *የህዝብ የመኪና ማቆሚያ ጋራጅ የመጀመሪያው-ፎቅ ላይ የሚገኘው የህዝብ መግቢያ በር ክፍት እንደሆነ ይቆያል*

**ሮክቪል፣ ሜሪላንድ፣ ጁላይ 1 ቀን፣ 2024 ዓ.ም**—በሜሪላንድ አውራ ጎዳና ላይ የሚገኘው በአሁን ሰዓት የካውንስሉ ጽህፈት ቤት ቢሮ ሕንፃ ላይ የሚገኘው የህዝብ መግቢያ በር ከጁላይ 17 ቀን ፣ 2024 ዓ.ም ጀምሮ የሕንፃው ዋና መግቢያ በር ላይ ተዘዋውሯል። የሕንፃው ሁለተኛ ፎቅ ላይ እየተከናወነ ባለው ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎች ጥገና በሚከናወንበት ሰዓት፣ ለነዋሪዎች እና ለመስሪያ ቤቱ ደህንነት ሲባል ለጊዜው የህዝብ መግቢያ በር እንዲቀየር መደረጉ አስፈላጊ ሆኗል። የግንባታው ስራ በጸደይ 2025 ዓ.ም ላይ ሲጠናቀቅ ጊዜ፣ ለህዝብ አገልግሎት የሚውለው ቦታ ለማህበረሰቡ ዓባላቶች እና ለጎብኚዎች የሚሆን የስብሰባ ቦታ እና ምግብን በሱቅ መልክ ያለ መቀመጫ ቦታ ለደንበኞች የሚሸጡ ሱቆች ይኖሩታል።

በዕድሳቱ ወቅት፣ ነዋሪዎች እና የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች የቀድሞ ካፍቴሪያ አጠገብ ከቡናማው ሸፍን ስር የሚገኘው የካውንስል ጽህፈት ቤቱ ሕንፃ ላይ ያለው የህዝብ መግቢያ በር ወደ በአቅራቢያው በሜሪላንድ አውራጎዳና ላይ የሚገኘው የካውንስሉ ጽህፈት ቤት ሕንፃ ማስታወቂያ ሰሌዳ ስር ያለው ዋና መግቢያ በር ላይ ተዘዋውሯል።

የካውንስሉ የጽህፈት ቤት ሕንፃ የመጀመሪያ ፎቅ ላይ የሚገኘው የህዝብ መግቢያ በር ክፍት እንደሆነ ይቆያል። ይሄ የመግቢያ በር የህዝብ መኪና ማቆሚያ ጋራጅ ጎን በአጎራባችነት ይገኛል። የህዝብ መኪና ማቆሚያ ጋርጅ መግቢያ በር በሮክቪል ውስጥ በ East Jefferson ጎዳና ላይ ወጣ ብሎ ይገኛል።

የካውንስሉ የጀነራል ሰሪቪስስ መምሪያ ቢሮ ነዋሪዎች እና ጎብኚዎች በቀላሉ ሁለቱንም የህዝብ መግቢያ ቦታዎችን በቀላሉ ማግኘት እንደሚችሉ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምልክት ጠቋሚ ሰሌዳዎችን አዘጋጅቷል።

# # #

<table>
<tr>
<td></td>
<td>
</td>
</tr>
<tr>
<td>በዕደሳት ወቅት በሜሪላንድ አውራ ጎዳና ላይ የሚገኘው የካወንስሉ ጽህፈት ቤት ሕንፃ መግቢያ በር።</td>
<td>ተደራሽነት ያለው የመጀመሪያ ፎቅ ላይ የሚገኘው የካውንስሉ ጽህፈት ቤት ቢሮ መግቢያ በር።</td>
</tr>
</table>